# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# 2ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

አንበሴ በቀለ

እሸቱ ኣጋ

**አርታኢ**

መላኩ ጽጌ

ትጃኒ ምትኩ

**ጥራት ተቆጣጣሪዎች**

በርናባስ ደበሎ

ይልፋሸዋ ጥላሁን

ታምሩ ገለታ

**ግራፊክስ**

ሰለሞን አለማየሁ ጉተማ

© 2014 ዓ.ም. የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ።

ይህ መፅሐፍ በ2014 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በትብብር የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የስዕሎችን የቅጂ መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ


| ይዘት | ገጽ |
| --- | --- |
| መቅድም | iv |
| መግቢያ | v |
| ሙዳየ ቃላት | vi |
| ምዕራፍ አንድ፡ ልብሶች | 1 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ ወቅቶች | 12 |
| ምዕራፍ ሶስት፡ ተረቶች | 23 |
| ምዕራፍ አራት፡ የአትክልት ቦታ | 37 |
| ምዕራፍ አምስት፡ የአካባቢ ጽዳት | 53 |
| ምዕራፍ ስድስት፡ ባህላዊ ሙዚቃ | 67 |
| ምዕራፍ ሰባት፡ መልካም ጠባይ | 82 |
| ምዕራፍ ስምንት፡ የምግብ ዝግጅት | 98 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ድጅታል መሳሪያዎች | 114 |
| ምዕራፍ አስር፡ የዱር እንስሳት | 132 |

# መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለው ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" በሚል ትኩረት ሰጥቶ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። በዚህም መሠረት ቀድሞ በነበረው ሥርዓትትምህርት ላይ ታይቶ የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ምርምር ተደርጓል። ከምርምሩ የተገኙ አቅጣጫዎችም የተማሪዎቹን ደረጃ አለመመጠን፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለመሆን፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠን እና ከተጓዳኝ ሥርዓትትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀም ናቸው። ስለሆነም ስርዓትትምህርቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ በአውድ የተደገፈ ለማድረግ፣ እና በተግባራዊ መማር ላይ የተመሠረተ የመማር ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ተቀርጿል።

ሥርዓትትምህርቱን መሠረት በማድረግም የትምህርት መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንዱ በመሆኑ ይህ አማርኛን እንደአፍመፍቻ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሊዘጋጅ ችሏል። መጽሐፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን ብቃት (Minimum Learning Competency)፣ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፣ እንዲሁም ተግባቦታዊ የመማር ዘዴን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው። ከዚህ አንፃር መጽሐፉ በቀድሞው የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ይሞላል ተብሎ ይጠበቃል።

## መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ አስር ምዕራፎች አሉት። እያንዳንዱ ምዕራፍ ደግሞ በሥሩ ስድስት ንዑሳን ትምህርቶችን አካቷል። እነዚህም ትምህርት አንድ ማዳመጥ፣ ትምህርት ሁለት መናገር፣ ትምህርት ሶስት ማንበብ፣ ትምህርት አራት መጻፍ፣ ትምህርት አምስት ቃላት እና ትምህርት ስድስት ሰዋስው ናቸው። እያንዳንዱ ትምህርት በመርሃ-ትምህርቱ በተደለደለው መሠረት በክፍለጊዜ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በሥሩ መመሪያዎችን፣ ትዕዛዛትን እና መልመጃዎችን ወይም ተግባራትን አካቷል። ከዚህ አኳያ የቋንቋ ክሂሎች የተደራጁት በቅድመ ተግባር፣ በጊዜ ተግባር እና በድህረ ተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ነው። የቋንቋ የዕውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ዘዴን ተከትለዋል። ከዚህ አንጻር የመማሪያ መጽሐፉ ማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንዲሆን ተደርጓል።

## ሙዳየቃላት

**መረዳት** (Comprehension)፡- የንግግርን ወይም የጽሑፍን ቋንቋ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ሂደት፣

**መነጠል** (Segmenting)፡- አንድን ሙሉ ቃል በቀለም ወይም በምዕላድ የመነጣጠል ሂደት

**መገመት** (prediction)፡- ከማንበብ/ከማዳመጥ በፊት ወይም በማንበብ/በማዳመጥ ሂደት ቀጥሎ ምን ሊመጣ ወይም ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፤

**ማጣመር** (blending)፡-በቀለሞች ወይም በምዕላዶች ተነጣጥሎ የቀረበን ቃል በአንድ ላይ አጣምሮ የመናገር፣ የማንበብ ወይም የመጻፍ ሂደት፣

**ቃላት በደቂቃ (ቃበደ)** (WPM)፡-በአንድ ደቂቃ በፍጥነት የተነበቡ ቃላት ብዛት፣ በአንድ ደቂቃ በትክክል የተነበቡ ቃላት ብዛት (WCPM ቃላት ትክክል በደቂቃ (ቃትበደ))፣ (የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ደረጃ ለመወሰን ያገለግላል።)

**ቅጥያ** (Affix)፡-በቃል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሚቀጠሉ ትርጉም አዘል ቅጥያዎች፣ (በቃል መጀመሪያ ሲቀጠሉ ቅድመአምድ ቅጥያ (Prefix)፣ በቃል መጨረሻ ሲቀጠሉ ድህረአምድ ቅጥያ (Suffix) ይባላሉ።)

# አማርኛ

**የቢጋር ሠንጠረዥ** (Graphic organizer)፡- የሀሳብን ግንኙነት በሥዕል ወይም በግራፍ ወይም በሠንጠረዥ የማደራጃ ስልት፣

**በትብብር መማር** (Cooperative learning)፡- አንድን የትምህርት ይዘት በጋራ እየተረዳዱ የመማር ሂደት፣

**ትክክለኛነት** (Accuracy)፡- አንድን ቃል፣ ሐረግ ወይም ዓረፍተነገር ያለስህተት የማንበብ ችሎታ፣

**አቀላጥፎ ማንበብ** (Fluency)፡- ፊደላትን፣ ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጭ በሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ፣

**አንብቦ መረዳት** (Reading comprehension)፡- አንድ ጽሑፍ አንብቦ ትርጉም የማግኘት ችሎታ፣

**አዳምጦ መረዳት** (Listening comprehension)፡- ንግግርን ወይም የሚነበብ ጽሑፍን አዳምጦ ተረድቶ ትርጉም የመስጠት ችሎታ፣

**ዐቢይ/ዋና ሀሳብ** (Main idea)፡- ከምንባብ ተጨምቆ የሚወጣ አንኳር መልዕክት፣

**ዐውድ** (Context)፡- ለአንድ እንግዳ ቃል ፍቺ ፍንጭ የሚሰጡ ከቃሉ በፊት ወይም በኋላ የሚገኙ ቃላት፣ ሐረጋት ወይም ዓረፍተነገሮች፣

# ምዕራፍ አንድ፡ ልብሶች

## ክፍለጊዜ፡ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የልብስ ዓይነቶች








## ክፍለጊዜ፡ ሁለት








## ክፍለጊዜ፡ ሶስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## የተማሪዎች የደንብ ልብስ








# የተማሪዎች የዘወትር ልብስ



## ክፍለጊዜ፡ አራት



## ክፍለጊዜ፡ አምስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### ሀ. መነጠል

1. ጨሌ



2. ብር



3. ጥጥ



4. ሰው



5. ጋቢ



6. ጦጣ



## ክፍለጊዜ፡ ስድስት

### ለ. ማጣመር

ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

| መነጠል | ማጣመር |
|---|---|
| ዛ - ፍ | ዛፍ |
| ጨ - ው | ጨው |
| በ - ር | በር |
| ነ - ጣ | ነጣ |
| ሶ - ፋ | ሶፋ |
| ጠ - ጣ | ጠጣ |

## ክፍለጊዜ፡ ሰባት

በምሳሌው መሰረት አጣምሩ።

ምሳሌ፡ ነ - ጭ ⟶ ነጭ

1. ነ - ጭ  2. ጥ - ጥ
2. ቀ - ይ  3. ስ - ር
3. ጥ - ሩ  4. ጥ- ሳ

## ክፍለጊዜ፡ ስምንት

# ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

ሀ. የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፡ __ ለጠ = በለጠ ፈለጠ ቀለጠ

1.__ ጠፈ

2.__ ገሰ

3.__ መድ

4.__ ረበ

5.__ ከረ

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

ለ. የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፡ አጠ__ = አጠበ አጠፈ አጠረ

1.ጠረ__

2.በቀ__

3.ገመ__

4. ደብተ__

5. ጠመ__

## ክፍለጊዜ አስር

ሐ. የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፡ ሰ__ ዳ = ሰሌዳ

1. ቦ___ ሳ
2. ጠረ___ ዛ
3. እ___ ሳስ
4. ደብ ___ ር
5. ብ ___ ር

# ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## የአሚና ልብስ



አሚና ባህላዊ ልብስ ለብሳለች። አሚና መቀነት ታጥቃለች። አሚና የለበሰችው ልብስ ነጭ ነው። ልብሷ ከጥጥ የተሰራ ነው። አሚና በጨሌ የተዋበ ቆሪ ይዛለች። ጨሌው

ሰማያዊ፣ ቀይ፣ ነጭና ጥቁር ነው። ባጠቃላይ በጣም ተውባለች።

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

ባዶ ቦታውን በተሰጡት ቃላት አሟሉ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቆሪ | መቀነት | ነጭ | ባህላዊ | ጥጥ |

1.አሚና ______ ልብስ ለብሳለች።

2.አሚና ______ ታጥቃለች።

3.የአሚና ልብስ ቀለም ______ ነው።

4.የአሚና ልብስ ከ______ የተሰራ ነው።

5.አሚና በጨሌ የተዋበ ______ ይዛለች።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት ድምጽ በማሰማት ተራ በተራ አንብቡ።

1. ባህላዊ

4. ቆሪ

2. ቡሉኮ
3. መቀነት
5. ተውባለች
6. ታጥቃለች

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

ለ. አረፍተነገሮቹን ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች ደጋግማችሁ አንብቡ።

1. ኮት ዘመናዊ ልብስ ነው።
2. በባህል ልብስ ተውባለች።
3. ጋቢ ከጥጥ ይሰራል።
4. የአንገት ልብስ ለብሳለች።
5. ቡሉኮ ባህላዊ ልብስ ነው።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

ድምፅ በማሰማት በተራ አንብቡ።


### የአሚና ልብስ

አሚና በባህላዊ ልብስ ተውባለች። የአሚና

ልብስ ነጭ ነው። በጨሌ ያጌጠ ቆሪ ይዛለች። ጨሌዎቹ ነጭ፣ ጥቁር፣ ቀይ ቀለማት አሉት።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

ቃላቱን ከስእሎቹ ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ቀሚስ | ሀ.  |
| 2. ሹራብ | ለ.  |
| 3. ኮት | ሐ.  |
| 4. ሸሚዝ | መ.  |
| 5. መቀነት | ሠ.  |

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ትምህርት ስድስት፡ መፃፍ

ሀ. ዐረፍተነገሮቹን አንብቡ።

1.ቢፍቱ ጎበዝ ተማሪ ናት

2.ተማሪዎቹ ተባብረው ያጠናሉ

3.ቤትህ ከዚህ ምን ያህል ይርቃል

4.የቤት ሥራችሁን ሰርታችኋል

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

ለ. ዐረፍተነገሮቹን ጻፉ።

1.ቢፍቱ ጎበዝ ተማሪ ናት።

2.ተማሪዎቹ ተባብረው ያጠናሉ።

3.ቤትህ ከዚህ ምን ያህል ይርቃል?

4.የቤት ሥራችሁን ሰርታችኋል?

ሐ. መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በትክክል ጻፉ።

# ምዕራፍ ሁለት፡ ወቅቶች

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የወላጆች ቀን






1.የተማሪ ወላጆች በ __________ ቀን ትምህርት ቤት ተገኝተዋል።

2.ተሸላሚ ተማሪዎች __________ ሊቀበሉ ቆመዋል።

3.ከተሸላሚዎቹ አንዷ __________ ናት።

4.ሳፊዬ __________ ተማሪ ናት።

5.በለጡ የጎበዘችው ከሳፊዬ ጋር ________ ከጀመረች በኋላ ነው።

## ክፍለጊዜ ሁለት



## ክፍለጊዜ ሦስት

ከቃላቱ ምረጡና ባዶ ቦታዎቹን አሟሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ውጤት | ሽልማት | ማጥናት |
| ወቅቶች | በጋ | ዕለት |

1.ለጎበዝ ተማሪዎች________ ተሰጠ።

2.ልጁ ከጓደኛው ጋር ______ ከጀመረ በኋላ ጎበዘ።

3.ተማሪዋ የተሸለመችው ከፍተኛ_______ አምጥታ ነው።

4.አንድ አመት አራት ______ አሉት።

5.ከወቅቶች ውስጥ አንዱ ______ ነው።

6.የወላጆች ቀን የተከበረው ቅዳሜ ______ ነው።

## ክፍለጊዜ አራት

### ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### መልመጃ አንድ

መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተራ በተራ በቃል መልስ ስጡ።



## ክፍለጊዜ አምስት

### መልመጃ ሁለት

ያለፈውን እሁድ ምን በመስራት እንዳሳለፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

### ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

ሀ. ከታች ያሉትን ቃላት ድምጽ በማሰማት ነጥላችሁ ተናገሩ።

ምሳሌ፡ ወቅት    ወ    ቅ    ት

1.በልግ    3. ሐምሌ

2.ወራት    4. ሀሙስ

## ክፍለጊዜ ሰባት

ለ. ፊደላትን አጣምራችሁ ቃላት አንብቡ።

1. ሰ - ፈ- ፎ    3. በ - ኋ - ላ

2. ስ - ን - ቋ    4. ሀ - ያ - ኗ

## ክፍለጊዜ ስምንት

### ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

ሀ. የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፡ ___ ለጠ = ገለጠ  መለጠ  በለጠ

1.___ ፃፍ
2.___ ሌዳ
3.___ ብተር
4.___ ለም
5.___ ግለፀ
6.___ ረም

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

**ለ. የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።**

ምሳሌ፡ መጻ___ = መጻፍ

1. ቦር___
2. መቀ___
3. መቅረ___
4. መል___
5. ጥያ___
6. ጠረጴ___

## ክፍለጊዜ አስር

**ሐ. የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።**

ምሳሌ፡ ሰ___ ዳ = ሰሌዳ

1. ጥ___ቄ
2. መ___ስ
3. ወን___ር
4. እር___ስ
5. ዶ___ተር
6. መል___

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

**መ.በምሳሌው መሠረት ለውጣችሁ ተናገሩ።**

ምሳሌ፡ ሮጠ ብሎ ይሮጣል ካለ፣

1. ፈለገ ብሎ → ይፈልጋል ይላል።
2. ለወሰ ብሎ→ _____ ይላል።
3. መለሰ ብሎ→ _____ ይላል።
4. ወደቀ ብሎ→ _____ ይላል።

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

**ትምህርት አምስት፡ ማንበብ**

**ድልድይ**



ምስል አንድ



ምስል ሁለት

የገቢሳና የድባቤ ቤተሰቦች ማዶ ለማዶ ናቸው። ገቢሳና ድባቤ የሚዋደዱ ባለትዳሮች ናቸው። ወላጆቻቸውም ይዋደዳሉ። በክፉም በደጉም አይለያዩም። በክረምት ግን ያቅራቢያቸው ወንዝ ያለያያቸዋል።

ችግሩን ለመፍታት ምን የሚያደርጉ ይመስላችኋል?

አንድ ቀን ሁለቱ ቤተሰብ ስለችግሩ ተወያዩ። በእነሱ ሀሳብ መነሻነት ያከባቢው ሰው ስብሰባ ተቀመጠ። በድልድይ

አስፈላጊነት ላይ ተነጋገሩ። ድልድይ ለመስራትም ተስማሙ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

**ባዶ ቦታውን በተሰጡት ቃላት አሟሉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ችግር | ድልድይ | ውይይት |

1.ወንዝ ለመሻገር ______ያስፈልጋል።

2.ለችግር መፍትሄ በ_____ይገኛል።

3.በወንዝ ምክንያት መለያየት__ ነው።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

**ጥያቄዎቹን በምንባቡ መሰረት መልሱ።**

1. ሁለቱን ቤተሰብ ያለያየው ምንድነው?
2. የድልድይ ስራ መነሻ ሀሳቡ የማንነው?
3. ከዚህ ምንባብ ምን ተረዳችሁ?

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

**ሀ. የሚከተሉትን ቃላት ድምጽ በማሰማት ተራ በተራ አንብቡ።**

1. ቤተሰቦች
2. የሚዋደዱ
3. ባለትዳሮች
4. ወላጆቻቸው
5. አቅራቢያቸው
6. ያለያያቸው

**ለ. አረፍተነገሮቹን ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች ደጋግማችሁ አንብቡ።**

1. ውይይት ችግር ለመፍታት ያስችላል።
2. በጋራ ማቀድ ለውጤታማነት ያበቃል።
3. በመተባበራቸው ውጤታማ ሆኑ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

**የሚነበቡላችሁን ቃላት በትክክል ፃፉ።**

1. ጠመኔ
2. መፅሐፍ
3. መምህር
4. መልመጃ

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ትምህርት ስድስት፡ መፃፍ

### ሀ. የሚከተለውን ፅሁፍ አንብቡ።

እሁድ የቤት ስራ ሰራሁ ሰኞ ለመምህሬ አሳየሁ መምህሬ ሁሉንም ጨረስክ አሉኝ እኔም አዎ አልኳቸው

### ለ. የሚከተለውን ፅሁፍ አንብቡ።

እሁድ የቤት ስራ ሰራሁ። ሰኞ ለመምህሬ አሳየሁ። መምህሬ፣ "ሁሉንም ጨረስክ?" አሉኝ። እኔም አዎ አልኳቸው።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### ትምህርት ስድስት፡ መፃፍ

እየተወያያችሁ ሀሳቡን ሙሉ አድርጉት።

ተማሪዎቹ በጋራ በማጥናታቸው____::

ወላጆቻቸውም ባመጡት ውጤት ደስተኛ ___:: በዚህም በጋራ___ለውጤት _ተገነዘቡ::


# ምዕራፍ ሶስት፡ ተረቶች

## ክፍለጊዜ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## ጠጣና አዞ





## ክፍለጊዜ ሁለት

### መልመጃ አንድ

**ያዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች**

**ሀ. ባዳመጣችሁት ታሪክ መሰረት መልሱ።**

1.ባለታሪኮቹ እነማን ናቸው?

2.ጠባዋ ካመለጠች በኋላ ምን አደረገች?

3.ጠባዋ ዘዴው ባይመጣላት ምን ትሆን ነበር?

**ለ. ቀጥሎ ባሉት አረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍቺ የሚሆኑ ከተሰጡት ቃላት ውስጥ ምረጡ።**

| | | |
|---|---|---|
| ዘዴ | የምር | ሳይስማሙ |
| ደረሰባት | አመራች | |

1.የጠባ ልጅ ግቤን ለማየት ወደዛው አቀናች።

2.ጠባ ዛፍ ላይ ወጥታ ከአንጀቷ ሳቀች።

3.ምክር ባለመስማቷ አደጋ ላይ ወደቀች።

4.ማምለጫ መንገድ ፈለገች።

5.እናትና ልጅ ቢማከሩም ሳይግባቡ ቀሩ።

## ክፍለጊዜ ሦስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

ካዳመጣችሁት ታሪክ ውስጥ ዋና ዋናውን ተራ በተራ ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ አራት

### ተግባር ሁለት

1. የምታውቁትን ተረት ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።
2. ጠጣዋ ከአዞው ለማምለጥ የተጠቀመችው ዘዴ ምን እንደነበር ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር ሦስት

የትምህርት ሰዓት ቢያልፍባችሁ ምን ዘዴ ትጠቀማላችሁ። ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተነጋገሩ። የተነጋገራችሁበትን ለክፍላችሁ ተማሪዎች ንገሩ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

**ትምህርት ሶስት፡ መነጠል እና ማጣመር**

### መልመጃ ሁለት

ሀ. የሚከተሉትን በመነጠል ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

1. እናት
2. ዘመድ
3. ምግብ
4. ወንዝ
5. ማየት

## ክፍለጊዜ ሰባት

ለ. የሚከተሉትን በማጣመር ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

1. ማ የ ት
2. ሰ ፈ ር
3. ደ ገ መ
4. ተ ጎ ጂ
5. አ ደ ጋ

## ክፍለጊዜ ስምንት

### ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

**መልመጃ ሶስት**

የሚከተሉትን ቃላት ከምስል ጋር አዛምዱ

| ቃላት | ምስል |
|---|---|
| ሰሌዳ |  |
| ጠመኔ |  |

| | |
|---|---|
| ላጲስ |  |
| መቅረጫ |  |
| መፅሐፍ |  |

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## መልመጃ አራት

**መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ድምጽ በመተው ተናገሩ።**

**ሀ. የቃል መነሻ ድምጽ በመተው ተናገሩ።**

**ምሳሌ “አጠና” “አ-” ቢተው “ጠና” ይሆናል።**

**“ጠና” መልስ ይሆናል።**

## ክፍለጊዜ አስር

**ለ. የቃል መጨረሻ ድምጽ በመተው ተናገሩ።**

ምሳሌ “መጣች” -“ች” ቢተው “መጣ” ይሆናል።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

ሐ. ከቃል መሃል ፊደል በመተው ተናገሩ።

ምሳሌ “አደረሰ” ከሚለው -“ደ” ቢተው “አረሰ” ይሆናል።”ረ” ቢተው “አደሰ” ይሆናል

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አራት፡ ማንበብ

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. ከጥንቸልና ከኤሊ ማን ይፈጥናል?
2. በአካባቢያችሁ ምን ምን አይነት እንስሳት አሉ?

# የኤሊና የጥንቸል ውድድር

አንድ ቀን ኤሊና ጥንቸል መንገድላይ ተገናኙ። ጥንቸልም ኤሊን" አንቺ ቀርፋፋ ወዴት ትሄጃለሽ?" አለቻት። ኤሊም ተናደደችና ከፈለግሽ ነይ በሩጫ እንወዳደር" አለቻት። ጥንቸሏም እሺ አለቻትና በሩጫውም ቦታ ተስማሙ። ቀበሮንም ዳኛ አደረጉት። ከዚህ በኋላ ቀበሮ አንድ ሁለት ሶስት አለና ሩጫውን አስጀመረ።

1. ኤሊና ጥንቸል ምን አይነት ውድድር ለማድረግ ተስማሙ?
2. ማን የሚያሸንፍ ይመስላችኋል?

ጥንቸል በአንድ ጊዜ ኤሊን ቀደመቻት። ዞር ብላ ኤሊን ስትንቀረፈፍ አየቻት። በጣም ሩቅ መሆኗን ስላወቀች አትደርስብኝም ብላ

ሳር ላይ ጋደም አለች። እንቅልፍም ወሰዳት። ኤሊ ቀስ እያለች ሄዳ ውድድሩን ጨረሰች። ተመልካቾችም ለኤሊ ሲያጨበጭቡላት ጥንቸል ከእንቅልፏ ነቃች። ጥንቸሏም መሸነፏን አውቃ ኤሊን ሁለተኛ ላለመስደብ ቃል ገባች።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

### የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አምስት

ሀ. የሚከተሉትን እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ኤሊ ጥንቸልን ሰደበቻት።
2. የውድድሩ ዳኛ ቀበሮ ነው።
3. ውድድሩን ያሸነፈችው ኤሊ ነች።
4. ተመልካቾቹ ያጨበጨቡት ለጥንቸል ነው።
5. ጥንቸል የተሸነፈችው በእንቅልፏ ምክንያት ነው።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

### ለ. ከሚከተሉት ቃላት መርጣችሁ ባዶ ቦታዎቹን አሟሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ከእንቅልፏ | በሩጫ | ሩጫውን |
| ጋደም | ቀርፋፋ | |

2. ኤሊ ተናደደችና ጥንቸልን ነይ_____ እንወዳደር" አለቻት።
3. ቀበሮ በዳኛነቱ______አስጀመረ።
4. ጥንቸል ሳር ላይ ______አለች።
5. ተመልካቾችም ለኤሊ ሲያጨበጭቡላት ጥንቸል______ነቃች።

# ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## አቀላጥፎ ማንበብ

የሚከተለውን የምንባብ ክፍል በፍጥነት እና በትክክለኛ አገላለጽ አንብቡ።

አንድ ቀን ኤሊና ጥንቸል መንገድላይ ተገናኙ። ጥንቸልም ኤሊን" አንቺ ቀርፈፋ ወዴት ትሄጃለሽ?" አለቻት። ኤሊም

ተናደደችና ከፈለግሽ ነይ በሩጫ እንወዳደር" አለቻት። ጥንቸሏም እሺ አለቻትና በሩጫውም ቦታ ተስማሙ። ቀበሮንም ዳኛ አደረጉት። ከዚህ በኋላ ቀበሮ አንድ ሁለት ሶስት አለና ሩጫውን አስጀመረ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### ተግባር አራት

**የሚከተሉትን አረፍተነገሮች አንብቡ።**

1. ጥንቸል በሩጫ ተሸነፈች።
2. ቀበሮ ሩጫውን አስጀመረ።
3. ተመልካቾቹ ለኤሊ አጨበጨቡ።
4. ኤሊና ጥንቸል መንገድ ላይ ተገናኙ።
5. በሩጫ ለመወዳደር ተስማሙ።
6. ጥንቸል ከእንቅልፏ ነቃች።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ትምህርት አምስት፡ መፃፍ

### መልመጃ ስድስት

**ከዚህ በታች ከተሰጡት ስርአተነጥቦች ውስጥ በመምረጥ አረፍተነገሩን አሟሉ።**

። ? !

1. ጎሽ እንኳን መጣህ
2. መቼ ትመጪያለሽ
3. ቤቱ ትልቅ ነው
4. የመፅሐፉ ዋጋ ስንት ነው
5. እሰይ ምኞቴ ተሳካ

## መልመጃ ሰባት

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በትክክል ፃፉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ ስምንት

ሀ. አራት ባለሁለት ፊደል ቃላት ጻፉ።

ለ. ሶስት ባለሶስት ፊደል ቃላት ጻፉ።

ሐ. ሁለት ባለአራት ፊደል ቃላት ጻፉ።

## ተግባር አምስት

ለአራት በመመካከር ስለአንድ አጭር ታሪክ የሚናገር አራት አረፍተነገር ፃፉ።

# ምዕራፍ አራት፡ የአትክልት ቦታ

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

## አትክልትና ፍራፍሬ



የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. አትክልት ምንድነው? ከፍራፍሬ በምን ይለያል?

2.አትክልትና ፍራፍሬ ምን ጥቅም ያላቸው ይመስላችኋል?

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ሀሳቦች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. ሁሉም የአትክልት አይነቶች ቅጠላቸው ይበላል።
2. አናናስ ፍሬያቸው ከሚበሉ ይመደባል።
3. አትክልትና ፍራፍሬዎች ተሸጠው ገንዘብ ያስገኛሉ።

## ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ ሁለት

የቀረቡትን አትክልትና ፍራፍሬዎች ቅጠላቸው፣ ፍሬያቸው እና ስራቸው የሚበላ ስር "✓" ምልክት በማድረግ ለዩ።

| አትክልትና ፍራፍሬ | ቅጠላቸው የሚበላ | ፍሬያቸው የሚበላ | ስራቸው የሚበላ |
|---|---|---|---|
| ጥቅል ጎመን | ✓ | | |
| ብርቱካን | | | |
| ካሮት | | | |
| ሰላጣ | | | |
| ሙዝ | | | |
| አንጮቴ | | | |
| ቆስጣ | | | |
| ማንጎ | | | |
| ድንች | | | |

## ክፍለጊዜ ሶስት

### ተግባር አንድ

1. በአካባቢያችሁ በምግብነት የሚዘወተሩ አትክልቶች ምን ምን እንደሆኑ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. በአካባቢያችሁ የሚበቅሉ የፍራፍሬ አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ አራት

### ተግባር ሁለት

አትክልትና ፍራፍሬዎች ያላቸውን ጠቀሜታ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩ። ከዚያም ያገኛችሁትን ሀሳብ ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ አምስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### መልመጃ ሶስት

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት እየነጠላችሁ አንብቡ።

ምሳሌ፡ ገንዘብ ገ ን ዘ ብ

1. አንሶላ
2. የሚበሉ
3. ክፍሎች
4. ማምረት
5. አናናስ

## ክፍለጊዜ ስድስት

ለ. የሚከተሉትን ድምጾች እያጣመራችሁ አንብቡ።

ምሳሌ፡ ገ ን ዘ ብ ገንዘብ

1. ይ ው ሳ ሉ

2. ይ በ ላ ል

3. ፍ ራ ፍ ሬ

4. ይ ሰ ጣ ሉ

5. ማ ም ረ ት

## ክፍለጊዜ ሰባት

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ አራት

ከተሰጡት ቃላት እየመረጣችሁ በቃል መልሱ።

| | | |
|---|---|---|
| ሜዳ | ኳስ | ፈተና |
| ሰልፍ | ባንዲራ | ቤተመጻህፍት |

1. የተማሪዎች ችሎታ የሚመዘንበት፣
2. ተማሪዎች ስፖርት የሚሰሩበት ቦታ፣
3. መጽሐፍ በፀጥታ የሚነበብበት ቦታ፣
4. ባንዲራ ለማውጣት የሚደረግ ስርአት፣

5. የአንድ አገር መለያ አርማ፣
6. ተማሪዎች የሚጫወቱበት ክብ ነገር፣

## ክፍለጊዜ ስምንት

## ድምጽ በመተው ማንበብ

## መልመጃ አምስት

ሀ. በምሳሌው መሰረት የመጀመሪያውን ድምጽ በመተው አንብቡ።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡ | ተሰራ | ሰራ |
| | ተሸለመ | ሸለመ |

| | |
|---|---|
| 1. አጸደቀ | 5. አማረ |
| 2. ከድምጽ | 6. ተማረች |
| 3. ተመለሰ | 7. ተተነተነ |
| 4. ተደገሰ | 8. መተካት |

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

ለ. በምሳሌው መሰረት አንድ ድምፅ ከመጀመሪያ በመጨመር አንብቡ።

ምሳሌ፡ ሰው ከሰው፣ በሰው፣

1.እርሳስ
2.መጣ
3.ጻፈ
4. ደረሰ
5. ሰሌዳ

## ክፍለጊዜ አስር

ሐ. በምሳሌው መሰረት ስሩ።

ምሳሌ፡ 1. ቡሬ ቡራቡሬ

2. ጅል ጅላጅል

1.ብልጥ
2.ገር
3.ጥሬ
4. ፍሬ
5. ቀይ
6. ረጅም

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

**መ. በጥንድ በመወያየት በምሳሌው መሰረት መነሻ ድምጽ በመነጠል ተናገሩ።**

ምሳሌ፦ 1. ተመረቀ → ተ_መረቀ

2. ተጠየቀ → ተ _ ጠየቀ

1. ተፃፈ 2. በዱላ 3. ከላጨ
4. በነገረ 5. ተመለሰ 6. በጨመረ

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

### ድምጽ መተካት

**ሀ. በምሳሌው መሰረት ከመጀመሪያ ያለውን ድምጽ በመተካት ስሩ።**

ምሳሌ፦ ከሰራ በሰራ

1. በሄደ 4. ደመረ
2. ከመጣ 5. ሰፈረ
3. ከበረ 6. ስብር

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

ለ. በምሳሌው መሰረት የቃላቱን የመሃል ፊደል በመተካት ሌላ ቃል መስርቱ።

ምሳሌ፡ አጠረ ⟶ አሰረ/አረረ/አፈረ

1. ቀነሰ
2. ቀበጠ
3. አጠና
4. አወራ

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

**ትምህርት አምስት፡ ማንበብ**

### የአትክልት ቦታ ዝግጅት





**የሚከተሉትን በቃል መልሱ።**

1. የአትክልት ቦታ እንዴት ይዘጋጃል?
2. ከምስሎቹ ስለቦታ ዝግጅት ምን ተረዳችሁ?

አትክልት ከመትከል በፊት ቦታ ማዘጋጀት ይገባል። ቦታ ሲዘጋጅ፣ አፈሩን ማመቻቸት ያስፈልጋል። አፈርን ለማመቻቸት ሰው ሰራሽና የተፈጥሮን ማዳበሪያ መጠቀም ይቻላል። የተፈጥሮ ከሚባሉት ውስጥ የከብት ፍግና የአትክልት ብስባሽ ይጠቀሳሉ። ሰው ሰራሽ የሚባለው ደግሞ በፋብሪካ ውስጥ የሚመረት ማዳበሪያ ነው። እነዚህን በመጠቀም የአፈርን ለምነት እንዲጨምር ማድረግ ይቻላል።

የተፈጥሮ ማዳበሪያ አፈር ውሃና ማዕድኖችን ይዞ እንዲቆይ ይረዳል። በተፈጥሮ ማዳበሪያ የዳበረ አፈር ጤናማ ተክሎችን ለማብቀል ተመራጭ ነው።

## አንብቦ መረዳት

### መልመጃ ሰባት

ሀ. የሚከተሉትን በቃል መልሱ።

1. አትክልት ከመትከል በፊት ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
2. አፈር ጤናማ ተክሎችን እንዲያበቅል ምን ያስፈልገዋል?
3. አፈርን ለአትክልት ምቹ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት?

# ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ለ. ከታች ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ምረጡና አረፍተነገሮቹን አሟሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማዳበሪያ | ምቹ | ለምነት | ሊበላሽ |
| ተመራጭ | ኖረው | | ማዕድኖችን |
| ለም | ተብላልቶ | | ማስዋብ |

1. የዳበረ አፈር ጤናማ ተክሎችን ለማብቀል ____ ነው።
2. አፈርን ለማመቻቸት ____ መጠቀም ይቻላል።
3. የተፈጥሮ ማዳበሪያ አፈር ውሃና _____ ይዞ እንዲቆይ ይረዳል።
4. ማዳበሪያን በመጠቀም የአፈርን _____ እንዲጨምር ማድረግ ይቻላል።
5. የቆሸሸን ቦታ በአበባ _____ ይቻላል።

6. ሰውየው በጥረቱ ያማረ ቦታ______።
7. ፍግ አፈርን___ ለማድረግ ይጠቀማል።
8. ጽዱ አከባቢን ለኑሮ ________ ነው።
9. ቆሻሻ ____ አፈር ሊያዳብር ይችላል።
10. በአያያዝ ጉድለት የአትክልት ጣእም ________።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### መልመጃ ስምንት

**በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆኑ ከ "ለ" ፈልጋችሁ አዛምዱ።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1.ለም | ሀ. ተፈላጊ |
| 2.ተመራጭ | ለ. የዳበረ |
| 3.ማመቻቸት | ሐ. በፋብሪካ የሚመረት |

4.የሚመረት     መ. ማስተካከል

5.ሰው ሰራሽ     ሠ. የሚሰራ

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ዘጠኝ

**የሚከተሉትን አረፍተነገሮች በየተራ አንብቡ።**

1.ግቢያችን ጠባብ ነው።

2.ባለችን ቦታ ላይ አትክልት እንተክላለን።

3. ከተከልናቸው ውስጥ አንዱ ሎሚ ናት።

4. ሎሚ ያለበት ጭማቂ ያስደስተኛል።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## ትምህርት ስድስት፡ መፃፍ

### መልመጃ አስር

የሚከተሉትን አረፍተነገሮች በተገቢ ምልክቶች አሟሉ።

1. በለጠ ኳስ ተጫወተ
2. እሮይ አረፍኩ
3. ክፍሉን ያፀዳው ማነው
4. ልጁ ጠንክሮ ስለሰራ ተሸለመ
5. በሬው በስንት ብር ተሸጠ
6. በሪቱ የት ሄደች

# ምዕራፍ አምስት፡ የአካባቢ ጽዳት

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የነአየለ ግቢ



የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. በምስሉ ላይ የሚታዩ ሰዎች ምን እያደረጉ ይመስላችኋል?
2. የግቢያችሁን ንጽህና እንዴት ትጠብቃላችሁ?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

| | | |
|---|---|---|
| አቆረ | ብክለት | ቃኘ |

1.የልብስ ማጠቢያው ውሃ ______

2.አየለ ግቢውን______

3.ፕላስቲክ ማቃጠል ያየር ______ ያስከትላል።

## ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1.አየለና ባለቤቱን ያሳሰባቸው ምንድን ነው?

2.የተጣለው ልብስ ማጠቢያ የምን መራቢያ ሆነ?

ለ. የሚከተሉትን እውነት ወይም ሀሰት

በማለት መልሱ።

1. እነአየለን ማታ ማታ ቢንቢዎች ያስቸግሯቸዋል:
2. እነአየለ የተጣለውን ልብስ ማጠቢያ ጥቅም እንዲሰጥ አደረጉ።
3. እነአየለ የፕላስቲክ ማጠቢያውን አቃጠሉ።
4. እነአየለ የተከሉት ዛፍ ነው።
5. ማጠቢያው በአፈር ሲሞላ ቢንቢዎቹ ጠፉ።

## ክፍለጊዜ ሶስት

ሐ. ባዳመጣችሁት መሰረት ባዶ ቦታዎቹን የሚያሟሉትን ቃላት በመምረጥ መልሱ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማጠቢያ | ማታ ማታ | ቢንቢ | ችግር |

1. አገልግሎት የማይሰጠው ልብስ ማጠቢያ ለ ________መራቢያ ሆኗል፡፡
2. ለነአየለ ግቢ መቆሸሽ ምክንያት የሆነው የተጣለ ልብስ ________ ነው፡፡
3. የልብስ ማጠቢያው ላይ የተራቡ ቢንቢዎች በነአየለ ላይ ____ፈጥረዋል፡፡
4. ቢንቢዎቹ እነአየለን የሚያስቸግሩት ________ ነው፡፡

**ክፍለጊዜ አራት**

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

በቤታችሁ አካባቢ በመጣላቸው ምክንያት ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በየተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ፡፡

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር ሁለት

በአካባቢያችሁ አገልግሎታቸው በማብቃቱ ከሚጣሉ ነገሮች ውስጥ በሌላ መልክ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ዘርዝሩ። ከዚያም ጥንድ ጥንድ በመሆን ባገኛችኋቸው ሃሳቦች ላይ ተወያዩባቸው። የተወያያችሁባቸውን ሃሳቦች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

**ለ. ሀሳብ አሰባስቡና ያገኛችሁትን ለክፍል ተማሪዎች አካፍሉ።**

የተጣሉና አከባቢን ሊበክሉ የሚችሉ

ነገሮችን ለዩ። የለያችሁትን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል አስቡ። እንዴት እንደሚወገድና ስራ ላይ ማዋል እንደሚቻል ያላችሁን ሀሳብ ለክፍል ተማሪዎች ንገሩ።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

**ሐ. ግቢያችሁ ቢቆሸሽ ምን ጉዳት የሚያመጣ ይመስላችኋል? ጉዳቱን እንዴት ማስቀረት ይቻላል? ሀሳባችሁን ለክፍል ተማሪዎች አካፍሉ።**

**ክፍለጊዜ ስምንት**

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

## መልመጃ ሁለት

ሀ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ድምጾች በፍጥነት ነጥላችሁ አንድ ባንድ ጥሩ።

1. ጽዳት
2. ቆሻሻ
3. ማጽዳት
4. ማሳመር
5. ማስዋብ

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

ለ. አጣምራችሁ አንብቡ

1. ቆ ሸ ሸ
2. ጽ ዳ ቷ
3. ግ ቢ ዋ
4. ሰ ፈ ሯ
5. አ ጽ ዱ

## ክፍለጊዜ አስር

## ትምህርት አራት፡ የቃል ጥናት

### መልመጃ ሶስት

ሀ. ከመነሻ የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፡ ___ ለጠ = ገለጠ መለጠ በለጠ

1. __ ተና
2. __ ልስ
3. __ ያቄ
4. __ ብተር
5. __ ጽሐፍ
6. __ ፍል

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

### ለ. ከመጨረሻ የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፡ መጽሐ__ = መጽሐፍ

1. ጥያ__
2. ወንበ__
3. ክፍ __
4. እርሳ__
5. መቀ__
6. መልመ_

### ሐ. ከመሃል የጎደሉትን ፊደላት አሟሉ።

ምሳሌ፡ሰ__ዳ = ሰሌዳ

1. ቦ __ሳ
2. መ__ስ
3. ወን__ር
4. እር__ስ
5. ደ__ተር
6. መል_

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

### መልመጃ አራት

መምህር ከሚያነቡላችሁ ቃላት ውስጥ ድምጽ ወይም ፊደል በመተው ትጠራላችሁ።

ሀ. የመጀመሪያ ድምጽ/ፊደል በመተው ፈጥናችሁ ቃሉን ጥሩ።

ምሳሌ፡ “አጠና” ⟶ “ጠና”

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

ለ. የመጨረሻ ድምጽ/ፊደል በመተው ፈጥናችሁ ቃሉን ጥሩ።

ምሳሌ፡ መጣች መጣ

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

ሐ. የሚነበብላችሁን ቃል ከመሃል ፊደል

በመተው በፍጥነት ተናገሩ።

ምሳሌ "አደረሰ" ከሚለው ቃል ውስጥ

"ደ" ቢተው "አረሰ"

"ረ" ቢተው" "አደሰ"

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

መ. የሚነበቡላችሁን ቃላት ፊደል

በመተካት በፍጥነት ጥሩ (ተናገሩ)።

ምሳሌ 1. በራ ⟶ መራ/ሰራ

2. ወሰደ ወረደ/ወለደ

ሠ. ፊደላቱን ከሰንጠረዡ በመምረጥና

በማጣመር አስር ቃላት መስርቱ።

ምሳሌ፡ ጠ + ራ ⟶ ጠራ

| | | |
|---|---|---|
| አ | በ | ሰ |
| ረ | ጠ | መ |
| ስ | ኖ | ራ |

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ትምህርት አምስት፡ማንበብ

### መልመጃ አምስት





ምስሉን በመመልከትና ከልምድ በመነሳት የሚከተሉትን በቃል መልሱ።

1. ከምስሉ ምን ተረዳችሁ?
2. ያካባቢ ንጹህ መሆን ምን ጠቀሜታ

አለው ትላላችሁ?

አካባቢን በንጽህና መያዝ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። ከነዚህ ውስጥ አካባቢን ንጹህ ያደርጋል። ንጹህ አከባቢ እይታን ይማርካል፤ ለመዝናኛነትም ያገግላል። የሚያዝናና ቦታ አእምሮን ለማዝናናትም ይጠቅማል።

በሌላ በኩል ያከባቢ ንጹህ አለመሆን የጤና መታወክን ያስከትላል። የጤና መታወክ የብዙ ተያያዥ ችግሮች ምክንያት ይሆናል። ስለዚህ አከባቢን ከቆሻሻ ማጽዳት የራስንም ጤና መጠበቅ ነው።

## መልመጃ ስድስት

### ያንብቡ መረዳት ጥያቄዎች

**የሚከተሉትን ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1. የአከባቢ ንጹህ አለመሆን የጤና መታወክ ያስከትላል።
2. የአከባቢ ንጹህ አለመሆን ከጤና ጋር ግንኙነት የለውም።
3. አካባቢን በንጽህና መያዝ የራስንም ጤና መጠበቅ ነው።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ሰባት

**የሚከተሉትን አረፍተነገሮች በፍጥነትና በትክክል በየተራ አንብቡ።**

1. ሌሎ መጣች።
2. ሌሎ መጣች?
3. ሌሎ መጣች!
4. በለጠ ጎበዝ ተማሪ ነው።

5.ስድሴ የሰራችው ስዕል ያምራል።

6.የቤት ስራችሁን ሰርታችኋል?

7.አንደኛ የወጣችው ማንናት?

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ

### ተግባር ሶስት

ሀ. መምህር የሚያነቡላችሁን ቃላት በትክክል ጻፉ።

ለ. በቡድን መጻፍ

መምህር በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በአነስተኛ ቡድን ተከፈሉ። ከዚያም የሚቀጥለውን ሀሳብ በተመለከተ ከአምስት አረፍተ ነገር ባልበለጠ አጭር ጽሁፍ አዘጋጁ። የግል ንጽህናችሁን እንዴት እንደምትጠብቁ

# ምዕራፍ ስድስት፡ ባህላዊ ሙዚቃ

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ

### ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች



## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ከላይ በስእል ከቀረቡት የሙዚቃ መሳሪያዎች የትኞቹን እንደምታውቁ ለመምህራችሁ ንገሩ።
2. ከላይ በስእሉ የቀረቡት የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚያወጡትን ድምጽ አስመስሉ።

## የማዳመጥ ጊዜ ክንውን

ከተሰጡት ቃላት መርጣችሁ በማስገባት ባዶ ቦታዎቹን አሟሉ።

| የክር | የትንፋሽ | የምት |
|---|---|---|

1. ከበሮ፣ ነጋሪት እና አታሞ______ መሳሪያዎች ናቸው።

2. ክራርና ማሲንቆ______ መሳሪያዎች
ናቸው።

3. ዋሽንት______ መሳሪያ ነው።

ክፍለጊዜ ሁለት

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

**ባዳመጣችሁት መሰረት ትክክል የሆነውን "እውነት"፣ትክክል ያልሆነውን "ሐሰት" በማለት መልሱ።**


1. ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከእንጨት፣ ከቆዳ ከጅማት ሊሰሩ ይችላሉ።
2. ዋሽንት ለመስራት ሸንበቆና ሹል ብረት ያስፈልጋል።
3. ፅናፅል ከክር የሚሰራ ነው።
4. ከበሮ ከእንጨትና ከቆዳ ሊሰራ ይችላል።

5. ማሲንቆ የትንፋሽ መሳሪያ ነው።

## ክፍለጊዜ ሶስት

## መልመጃ ሁለት

የሚከተለውን አሟሉ




## ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

በአካባቢያችሁ ስለሚዘወተር ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ በቡድን ተወያይታችሁ በተወካያችሁ አማከኝነት ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር ሁለት

ቃጭል፣ ጽናፅል እና ድቤ በባህላዊ ሙዚቃ ውስጥ እንዴት እንደሚያገለግሉ ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

### ተግባር ሶስት

በአካባቢያችሁ ስለሚታወቅ አንድ የሙዚቃ መሳሪያ ምንነትና ከምን ከምን እንደሚሰራ በቃላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

## ክፍለጊዜ ሰባት

**ትምህርት ሶስት፡ ማጣመርና መነጠል**

### መልመጃ ሶስት

በቃል ውስጥ ያሉ ድምጾችን ነጥላችሁ ጥሩ።

ነጥላችሁ የጠራችሁትን ወዲያው

አጣምራችሁ ቃሉን ተናገሩ።

1. ቁስ　　4. ቃጭል

2. ጭራ　　5. ጅማት

3. ክራር　　6. ጠፍር

ክፍለጊዜ ስምንት

## መልመጃ አራት

ቃላቱ ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር ተናገሩ።

ምሳሌ 1 ከበሮ　　በከበሮ/ስለከበሮ/እንደከበሮ

2. ደረደረ　　መደርደር/ደርዳሪ

3. ክራር　　4. መቃ

4. ጎሰመ　　5. ጽናፅል

5. ደወለ　　6. ቃጭል

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ አምስት

ቀጥሎ ካሉት ቃላት ጋር ተመሳሳይ ዜማ የሚፈጥሩ ቃላትን ተናገሩ።

ምሳሌ 1. ክህሎት አድናቆት/አገልግሎት

2. ህዳሴ ግስጋሴ/ልስላሴ

1. ብቃት
2. ስንፍና

## ክፍለጊዜ አስር

### መልመጃ ስድስት

የሚከተሉትን ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ በሚጀምሩና በሚጨርሱ ክፈሏቸው።

| | | |
|---|---|---|
| መዘመር | ውልቃት | መቀመር |
| እርማት | ግርፋት | መደመር |
| ምርቃት | ማንበብ | ሽልማት |
| መጻፍ | ውቅራት | መመለስ |
| መሳተፍ | እልባት | መማር |
| እርዛት | መራቆት | ብቃት |
| ጥራት | መነከር | |

| በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ | በተመሳሳይ ድምጽ የሚጨርሱ |
|---|---|
| መዘመር | ውልቃት |
| መደመር | ሽልማት |
| | |

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## መልመጃ ሰባት

ቅጥያ በመተው ጻፉና አንብቡ

ሀ. የመጀመሪያውን ቅጥያ መተው

ምሳሌ 1 በማሲንቆ ⟶ ማሲንቆ

2. ስለመታ ⟶ መታ

1. ስለጎሰመ 3. በነጋሪት

2. ስለነፋ 4. እንደዋሽንት

ለ. የመጨረሻውን ቅጥያ በመተው ማንበብ

ምሳሌ1. ከርካሪዎች ከርካሪ

1. ጎሳሚዎች 3. መቺዎች

2. ደርዳሪዎች 4. ገዝጋዦች

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

### ሰመረና ዋሽንት

1. ዋሽንት ምንድነው?
2. ከየትኛው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ይመደባል? ለምን?

ሰመረ ኀበዝ ተማሪ ነው። ባከባቢው ያሉ ነገሮችን መፈተሽ ይወዳል። በሰፈራቸው ታዋቂ ዋሽንት ነፊ ሰው ነበሩ። እኚህ ሰው የሚጠቀሙባትና አብራቸው የኖረች ዋሽንት ነበረቻቸው። አንድ ቀን ሰመረ ተጠግቷቸው በትኩረት ሲመለከት ቆየ። በኋላ እዲያሳዩት ጠየቃቸው። ከሸንበቆ እደሚሰራ ነገሩት። በአዋቂ እንዳሰሩና እንዳይሰበርባቸው እንደሚጠነቀቁ ነገሩት። ቢሰበር አሳምሮ የሚሰራላቸው ባለሙያም አለመኖሩን ነገሩት። ለምን አይሰራም የሚል ጥያቄ ተፈጠረበት።

## መልመጃ ስምንት

**የሚከተሉትን በምንባቡ መሰረት መልሱ።**

1. ሰውየው በደንብ ማየት ለምን ከለከሉት?

2. ሰመረ አገላብጦ ማየት ለምን ፈለገ?

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## አንብቦ መረዳት

### መልመጃ ዘጠኝ

**ከምንባቡ የወጡ አረፍተነገሮች የያዙትን ሀሳብ አብራሩ።**

1. ነገሮችን መፈተሽ ይወዳል።
2. አብራቸው የኖረች ዋሽንት ነበረቻቸው።
3. ተጠግቷቸው በትኩረት ሲመለከት ቆየ።
4. አገላብጦ እንዲያይ አልፈቀዱለትም።
5. በአዋቂ እንዳሰሩት ነገሩት።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## በጊዜ የተገደበ ንባብ

### መልመጃ አስር

## ለአንድ ደቂቃ በተቻለ ፍጥነት አንብቡ።

ማሲንቆ ከክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች መካከል አንዱ ነው። ማሲንቆ ለማዘጋጀት ብዙ የፈረስ ጭራዎች አንድ ላይ ይሸረባሉ። ከዚያ በኋላ ሣጥን መሰል ነገር በጣውላ ይዘጋጃል፤ ድምፅንም ለማጉላት በፍየል ቆዳ ይለጎማል። በተጨማሪም በሳጥኑ በአንደኛው ማዕዘን ውስጥ ቁልቁል አንድ ቋሚ እንጨት ይገባል። በቋሚው እንጨት ላይ የፈረስ ጭራው ይወጠራል። ሌላ ደጋን የመሰለ እንጨትም ይዘጋጃል። በዚህ እንጨት ላይም የፈረስ ጭራ ይወጠራል። ደጋኑና በቋሚ ላይ የተወጠረውን አንድ ላይ በመገዝገዝ የሙዚቃ ድምጽ ያወጣል።

# ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ

### መልመጃ አስራ አንድ

ከሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱን በቡድን ምረጡ። የመረጣችሁት የሙዚቃ መሳሪያ ከምን እንደሚሰራና የየትኛው የሙዚቃ መሳሪያ ክፍል እንደሆነ ተወያዩ። ተጨማሪ ከመሳሪያው ጋር የተያያዘ በማዳመጥ ጊዜ የያዛችሁትን ማስታወሻ ተመልከቱ። ከቡድን አባላት ሃሳብ አሰባስቡ። በተሰበሰቡ ነጥቦች ላይ ተወያዩ። የተወያያችሁበትን ሃሳብ አደራጁ። በተደራጀው ሃሳብ አጭር ታሪክ ጻፉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### ተግባር አራት

በቡድን የጻፋችሁትን አጭር ታሪክ በአንድ የቡድኑ አባል ይነበብ። የሚጨመርበት ወይም የሚቀነስ ካለ ሃሳብ ስጡበት። የተስማመችሁበትን የመጨረሻ ጽሁፍ አዘጋጁ።


## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ተግባር አምስት

መምህር በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ጽሁፉን ለሌሎች ቡድን አባሎች አንብቡ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

ሀ. የሚከተሉትን ክቦች በቃላት አሟሉ።




ለ. መምህር የሚያነቡላችሁን አረፍተነገሮች በትክክል ፃፉ።


ሐ. ከእያንዳንዱ የሙዚቃ መሳሪያ አይነት ሁለት ሁለት ጻፉ።

የክር    የትንፋሽ    የምት

# ምዕራፍ ሰባት፡ መልካም ጠባይ

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ



### አቶ ቶለሳ

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከስእሉ ምን እንደተረዳችሁ ተናገሩ።
2. መልካም ጠባይ መገለጫዎች ምን ምን ይመስሏችኋል?

## የማዳመጥ ጊዜ

መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ትርጉማቸውን የማታቋቸውን ቃላት ማስታወሻችሁ ላይ ጻፉ።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ባዳመጣችሁት ታሪክ መሰረት መልሱ።

1. ከሰማችሁት ታሪክ ምን መልካም ነገሮችን ተረዳችሁ።
2. አቶ ቶለሳ በመንገድ ላይ ያገኙት ሰው ምን አይነት ነው?
3. አቶ ቶለሳ ባለቤታቸውን ምን በማለት አሞገሷቸው?

## ክፍለጊዜ ሁለት

### ለ. ትክክለኛውን መልስ መርጣችሁ መልሱ።

1. የአቶ ቶለሳ መልካም ጠባይ በምን ይገለፃል

ሀ. ችግረኞችን በመርዳት

ለ. የተበደሩትን በመክልከል

ሐ. ሩህሩህ ባለመሆን

2. ችግረኛው ሰውዬ ያለበት ሁኔታ_____

ሀ. ልብሱ የተበጫጨቀ ነው

ለ. እግሮቹ በእንቅፋት ቆስለዋል

ሐ. ሁለቱም መልስ ናቸው

3. አንድ ቅያሪ ልብስ ካለን ይበቃናል ያሉት ማን ናቸው?

ሀ. አብደኔ　　ለ. ወይዘሮ አያንቱ

ሐ. አቶ ቶለሳ

4. ለተራበ ምግብ ከሆነ ለታረዘ______

ሀ. ውሀ ለ. መድኃኒት ሐ. ልብስ

5. ለ ______ የሚራራ ሰው መልካም ባህሪ ያለው ነው።

ሀ. ነዳያን ለ. ለጠገበ ሐ. ለሌባ

## ክፍለጊዜ ሶስት

## መልመጃ ሁለት

### የሚከተሉትን አዛምዱ

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ነዳያን | ሀ. መረዳዳት |
| 2. መታረዝ | ለ. መስጠት |
| 3. ማካፈል | ሐ. ድሆች |
| 4. መደጋገፍ | መ. ልዋጭ |
| 5. ቅያሬ | ሠ. መራቆት |

## ክፍለጊዜ አራት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

የመልካም ጠባይ መገለጫዎች ምን ምን እንደሆኑ በጥንድ ተወያዩ። ከዚያ የተስማማችሁበትን ለክፍልተማሪዎች ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር ሁለት

በአካባቢያችሁ በጥሩነታቸው የሚታወቁ ሰዎች ምን ምን ተግባራትን እንደሚፈጽሙ ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

### ተግባር ሦስት

መልካም ባህሪ ነው ከምትሉት ውስጥ አንዱን ምረጡ። የመረጣችሁትን መልካም ባህሪ ምንነትና የሚያስገኘውን ጥቅም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

## ክፍለጊዜ ሰባት

### ትምህርት ሶስት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ ሶስት

ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ባዳመጣችሁት መሰረት ፍቺ ስጡ።

1. ማካፈል
2. ተደጋግፎ
3. ታረዙ
4. ነዳይ
5. ደግ
6. ኮራሁብሽ

ለ. ቃላት ላይ ቅጥያ በመጨመር ተናገሩ።

ምሳሌ 1 ደግ ደግነት/ደጎች

2. መገበ /ስለመገበ/ እንደመገበ/

እየመገበ

1. መጸወተ 5. ምክር

2. ቸር 4. ራራ

## ክፍለጊዜ ስምንት

ሐ. ቀጥሎ ካሉት ቃላት ጋር ተመሳሳይ ዜማ የሚፈጥሩ ሶስት ሶስት ቃላት ተናገሩ።

**ምሳሌ 1. ፍጥነት ግድፈት/ብልጠት**

**2. ግስጋሴ ህዳሴ/ልስላሴ**

1. ርህራሄ 3. ውዝዋዜ

2. ሀዘኔታ 4. ደግነት

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

**መ. ቃላት ላይ ቅጥያ በመጨመር ተናገሩ።**

ምሳሌ 1.ክፉ ክፋት/እንዲከፋ/ስለከፋ

2. ረዳ መርዳት/እርዳታ/ስለረዳ

1. ብልጥ
2. ለገሰ
3. ደግ
4. አዘነ

### መልመጃ አራት

**የሚከተሉትን ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ በሚጀምሩና በሚጨርሱ ስር ደልድሏቸው።**

## ክፍለጊዜ አስር

**የሚከተሉትን ቃላት በተመሳሳይ ድምጽ በሚጀምሩና በሚጨርሱ ስር ደልድሏቸው።**

| | | |
|---|---|---|
| መመፅወት | ደግነት | መታዘዝ |
| እርዛት | ማገዝ | ቅናት |
| ምርቃት | ግንዛቤ | ሽልማት |
| ቸርነት | መደገፍ | በጎነት |
| መራቆት | መታቀፍ | ክፋት |

| በተመሳሳይ ድምጽ የሚጀምሩ | በተመሳሳይ ድምጽ የሚጨርሱ |
|---|---|
| መዘመር | ውልቃት |
| መታዘዝ | ሽልማት |
| | |

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አራት፡ ማንበብ

## የመልካም ስነምግባር መገለጫዎች

### ቅድመንባብ ጥያቄ

1. መልካም ስነምግባር ምንድን ነው?
2. የመልካም ስነምግባር መገላጫዎች ምን ምን ይመስሏችኋል?

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

**እያነበባችሁ የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች የሚያሟሉ ቃላት ፈልጉ።**

1. የመልካም ስነምግባር መገለጫዎች ሀቀኝነት፣ ሰውን ማክበርና______ናቸው።

2. አደራን ተቀብሎ በአግባቡ መያዝ_ ነው።

ሀቀኝነት፣ ሰዎችን ማክበርና ታማኝነት የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው። ሀቀኝነት ሲባል እውነትን መናገር፣ በእውነት መስራት፣ አለመዋሸት ማለት ነው።

ታማኝነት ደግሞ የተሰጠን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት፣ አደራን ተቀብሎ በአግባቡ መያዝ፣ የሰውን ንብረት ካልተፈቀደ በስተቀር አለመንካት፣ አለመስረቅና የመሳሰሉትን ድርጊቶች አለመፈፀም ናቸው። ሰዎችን ማክበር ሲባል ደግሞ አለመሳደብ፣ ለትልልቆች ቅድሚያ መስጠት፣ መታዘዝ፣ ጓደኛን መውደድ፣ ከራስ ይልቅ ለሰዎች ማሰብን ያጠቃልላል።

# አንብቦ መረዳት

## መልመጃ አምስት

**ሀ. በምንባቡ መሰረት መልሱ።**

1.ሀቀኝነት ሲባል ምን ምንን ያካትታል?

2.ታማኝ የሆነ ሰው ምን ምን ያደርጋል?

3.እውነትን መናገርና በእውነት መስራት የምን መገለጫዎች ናቸው?

## ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

**ለ. ቃላትና ሀረጋቱን በሚወክሉት ባህሪ ስር መድቡ።**

| | | |
|---|---|---|
| ሀቀኝነት | መስረቅ | ማስታረቅ |
| ጉቦ መቀበል | መሳደብ | ታማኝነት |
| መዋሸት | መታዘዝ | ሰውን ማክበር |
| ራስ ወዳድነት | | |

| ጥሩ ባህሪ | መጥፎ ባህሪ |
|---|---|
| ሀቀኝነት | መስረቅ |
| | |
| | |
| | |
| | |

## መልመጃ ስድስት

**መነሻና መድረሻ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት ከምንባብ ለይቶ ማውጣት**

**ሀ. መነሻ ቅጥያ ያላቸው ቃላት**

**ምሳሌ፡ የመልካም**

**ለ. መድረሻ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት**

**ምሳሌ፡ ሀቀኝነት**

# ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ተግባር አራት

የሚከተለውን ታሪክ በተገቢው ፍጥነት ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

## የአቶ ቶለሳ ባልንጀራ።

የአቶ ቶለሳ ባልንጀራ አቶ አደም ይባላሉ። አቶ አደም መልካም ሰው ናቸው። ችግረኞችን ይረዳሉ። ሀቀኛ መሆናቸውን ጎረቤቶቻቸው ይመሰክራሉ። የተቀያየሙ ሰዎችን ያስታርቃሉ። ለወጣቶች ልምድ ያካፍላሉ። ወጣቶችን ይመክራሉ። የሰው ንብረት አይነኩም። እንደ አቶ ቶለሳ ደግ ሰው ናቸው። ሀብትም አፍርተዋል።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

### ተግባር አምስት

ከላይ ያለውን ታሪክ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በትክክለኝነት አንብቡ።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### ተግባር ስድስት

የሚከተሉትን አረፍተነገሮች መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት አንብቡ።

1.መልካም መስራት ያስመሰግናል።

2.ጥሩ ስነምግባር ያለው ሰው ታወቃላችሁ።

3.የሚገርም ነው! እጅግ ተውበሃል!

4.ዋ! ይህቺን ትደግማትና ልብ አድርግ!

5.የቤት ስራ መስራት ጠቀሜታው ለራሳችን ነው።

6.መምህራችን ደብተር፣ መጽሐፍና ብዕር በስርአት እንድንይዝ መከሩን።

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ትምህርት አምስት፡ መጻፍ

### ተግባር ሰባት

ስለመልካም ስነምግባር ምንነትና ጠቀሜታ በቡድን ተወያዩ። የተወያያችሁበትን ዋና ዋና ነጥብ ማስታወሻ ያዙ። በቡድን የተያዘውን ማስታወሻ በመጠቀም አጭር ታሪክ ጻፉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### ተግባር ስምንት

በቡድን የጻፉችሁት በአንድ የቡድኑ አባል ይነበብ። የሚጨመርበት ወይም የሚቀነስ ካለ ሀሳብ ስጡበት። የተስማመችሁበትን የመጨረሻ ጽሁፍ አዘጋጁ።

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### ተግባር ዘጠኝ


መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ጽሁፉን ለሌላ ቡድን አባሎች አንብቡ።

# ምዕራፍ ስምንት፡ የምግብ ዝግጅት

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ማዳመጥ

## የተደራጀ ማዕድ ቤት





## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከላይ ከቀረበው ምስል ምን ተረዳችሁ? ማዕድ ቤት ምንድነው?

## ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ :አንድ

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**በአዳመጣችሁት መሰረት በቃል መልሱ።**

1. በማዕድ ቤት ውስጥ ምን ምን ነገሮች ይገኛሉ?
2. የምግብ ጥሬ እቃዎችንና መገልገያ እቃዎችን በንጽህና ለመያዝ ምን ያስፈልጋል?

## ክፍለጊዜ ሶስት

### መልመጃ:ሁለት

**መምህራችሁ ካስደመጧችሁ ምንባብ ውስጥ ዋና ዋና ነጥቦችን አደራጁ።**

## ክፍለጊዜ አራት

### መልመጃ :ሶስት

**“የተደራጀ ማዕድ ቤት” ከሚለው ምንባብ ለወጡ ቃላት ፍቺ ስጡ።**

ምሳሌ፡ ማጠብ ፡ ማጽዳት

1. ትንሽ
2. ማዘጋጀት
3. ቁሳቁሶች
4. ጥሬ እቃ

## ክፍለጊዜ አምስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

ሀ. የቤተሰቦቻችሁን ማዕድ ቤት እና ያዳመጣችሁትን ታሪክ በማነጻጸር የሚለያዩበትንና የሚመሳሰሉበትን በየተራ እየተነሳችሁ ለክፍል ተናገሩ፡፡

ለ. በማዕድ ቤት ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ቁሳቁሶችን በቡድን ተወያይታችሁ ለዩ። እየተነሳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

በውይይት የለያችኋቸውን የማዕድ ቤት ቁሳቁሶች አገልግሎታቸውንና ከምን

እንደተሰሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ።

**ክፍለጊዜ ሰባት**

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### መልመጃ አራት

**ሀ.መነሻ ቅጥያ መነጠል**

ምሳሌ፡ የተደራጀ  የ - ተደራጀ

1.በማዕድ  4. የሚያገለግሉ

2.ለማዘጋጀት  5. የተለያዩ

3.የምግብ

**ለ. መነሻ ቅጥያ ማጣመር**

**ምሳሌ፡ የ + ምግብ = የምግብ**

1. የ + ግድ =

2 በ + ጽዳት=

3. የ + ሽንኩርት=

4. ከ + ድስት=

5. በ + ማንኪያ=

## ክፍለጊዜ ስምንት

## መልመጃ አምስት

### ሀ. መድረሻ ቅጥያውን ነጥሉ

ምሳሌ ፡ ልጆች = ልጅ ኦች

1. ምግቦች
2. ቁሳቁሶች
3. ሳህኖች
4. እቃዎች
5. ቢላዎች

### ለ. ቃላትን ከመድረሻ ቅጥያዎች ጋር አጣምሩ።

ምሳሌ፡ ስንዴ + ው = ስንዴው

1. ቀረ + ሁ = ________
2. በላ + ን = ________

3.ወሰደ + ች = ________

4.ሀገር + አችን = ________

5.ቤት + አቸው = ________

**ክፍለጊዜ ዘጠኝ**

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ ስድስት

ሀ. በተሰጡት ቃላት ውስጥ ያሉ ፊደላትን ቦታ በመቀያየርና በመቀነስ የተለያዩ ቃላት መስርቱ።

**ለምሳሌ፡ ሰለጠነ፣ ሰጠ፣ ነጠለ**

1. አበሰለ
2. ቀላቀለች
3. አቀረበ
4. ዘይት

## ክፍለጊዜ አስር

ለ. በ "ሀ" ስር ያሉትን በ"ለ" ስር ካሉት ቅጥያዎች ጋር አዛምዱ።

| ተ.ቁ | "ሀ" | "ለ" |
|---|---|---|
| 1 | ወሰደች | ሀ.ተ- |
| 2 | መጣሽ | ለ.ከ- |
| 3 | ተሰራ | ሐ.ስለ- |
| 4 | ከአህመድ | መ.-ሽ |
| 5 | ስለመጣ | ሠ. -ች |

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት ተመሳሳይ ዜማ የሚፈጠሩ ቃላትን መስርቱ

ምሳሌ፡ 1. ቁርጠት 2. ግንባታ

ብልጠት እርባታ

# ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

## የዶሮ ወጥ አሰራር

### የቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. የዶሮ ወጥ ለመስራት ምን ምን እንደሚያስፈልግ ለመምህራችሁ ንገሩ።
2. በአካባቢያችሁ በበዓል ጊዜ ምን አይነት ምግብ ይዘጋጃል?

### የንባብጊዜ ጥያቄዎች

**የቀረበላችሁን ምንባብ እያነበባችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የዶሮ ወጥ ለመስራት_____ የዶሮ ስጋ በርበሬና ቅቤ ያስፈልጋል።
2. ሽንኩርቱ _____ይከተፋል።

የዶሮ ወጥ ለማዘጋጀት የተለያዩ ነገሮች ያስፈልጋሉ። እነርሱም፡ የዶሮ ስጋ፣ ሽንኩርት፣ በርበሬ፣ ዘይት፣ ቅቤና ቅመማቅመሞች ናቸው። የዶሮ ወጥ የራሱ የሆነ የአዘገጃጀት ስርአት አለው። በመጀመሪያ በርከት ያለ ሽንኩርት ደቆ ይከተፋል።

የተከተፈው ሽንኩርት ዘይት ሳይገባበት በደንብ ይቁላላል። በመቀጠል በርበሬ ከሽንኩርቱ ጋር አብሮ እንደገና በደንብ ይታሻል። እንዲሁም ዘይት ይገባና ትንሽ ከሽንኩርቱና ከበርበሬው ጋር እንዲበስል ይደረጋል። ከዚያም ታጥቦ የተዘጋጀው የዶሮ ስጋ ተጨምሮ እስኪበስል ድረስ ይቁላላል።

በመጨረሻም ይከለስና ቅቤና ቅመማቅመሙ ተስተካክሎ ለመመገብ ዝግጁ ይሆናል።

## አንብቦ መረዳት

### መልመጃ ሰባት

በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።

1. የዶሮ ወጥ ለመስራት ምን ምን ያስፈልጋል?
2. በዶሮ ወጥ ዝግጅት ውስጥ የመጨረሻው ሥራ ምንድነው?
3. ከምንባቡ ምን ተረዳችሁ?

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

### ተግባር ሁለት

## ባህላዊ ምግቦች

በሀገራችን ብዙ ባህላዊ ምግቦች አሉ። እንጀራ፣ ገንፎ፣ ጨጨብሳ፣ ቅንጬ፣ ዶሮ

ወጥ፣ ሽሮ ወጥ፣ ወዘተ ናቸው።በአለማችን ውስጥ እንጀራ የባህል ምግብ የሆነው በእኛ ሀገር ብቻ ነበር። በአሁኑ ዘመን የውጭ ሀገር ሰዎችም እንጀራ መብላት ጀምረዋል። ይህም የባህል ምግባችን ታዋቂ እየሆነ መምጣቱን ያሳያል።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

**ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ**

**መልመጃ ስምንት**

**“የዶሮ ወጥ አሰራር” በሚለው ምንባብ ውስጥ ያለውን የድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ጻፉ።**

**ምሳሌ** 1. ሽንኩርት መክተፍ

2. ማቁላላት

1. ሸንኩርት መክተፍ
2. ማቁላላት
3. ቅቤ መጨመር
4. የተዘጋጀ የዶሮ ስጋ መጨመር
5. መከለስ
6. ዘይት መጨመር
7. በርበሬና ሸንኩርት አብሮ ይታሻል

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

### መልመጃ ዘጠኝ

ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ቃላት በማገናኘት አረፍተ ነገሮች ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ገመቹ | ዶሮ ወጥ | ሰራች |
| ጫልቱ | | በላች |
| መሀመድ | | በላ |
| | | ሰራ |

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### መልመጃ አስር

**ጥያቄዎቹን በቃል መልሱ።**

1. ስለምታውቁት ባህላዊ ምግብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ከባህላዊ ምግቦች የምትወዱትንና ለምን እንደምትወዱት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስራ አንድ

**ቃላቱን ከስዕሎቹ ጋር አዛምዱ።**

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ፓስታ | ሀ.  |
| 2. ገንፎ | ለ.  |
| 3. ክትፎ | ሐ.  |
| 4. ጨጨብሳ | መ.  |
| 5. ዶሮ ወጥ | ሠ.  |

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

### መልመጃ አስራ ሁለት

**ቅጥያዎችን ከቃል ጋር አጣምራችሁ ፃፉና አንብቡ።**

ምሳሌ፡- አል-መጣም፡- አልመጣም

1. ስለ-ቀረ 2. ከ-ወጣ

3. የ-ሰው 4. በ-በሬ

## መልመጃ አስራ ሶስት

የምትወዱትን የምግብ አይነት ጥቀሱ።

አዘገጃጀቱን ጻፉ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ድጅታል መሳሪያዎች

## ክፍለጊዜ አንድ

### ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### ድጅታል መሳሪያ



### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ከስዕሉ ምን ትረዳላችሁ?
2. ከስዕሉ ላይ ያሉት መሳሪያዎች አገልግሎት ተናገሩ።

## መልመጃ አንድ

ሀ. አዳመጣችሁ በምታገኙት መረጃ ባዶ ቦታዎቹን የሚያሟሉ መልሶች በቃል ስጡ።

1. መዘመን ተግባቦትን _____ አድርጎታል።
2. ፌስቡክ _____ መጠቀም ተችሏል።
3. ተንቀሳቃሽ ስልክ _____ ማውራት አስችሏል።

## ክፍለጊዜ ሁለት

## መልመጃ ሁለት

ሀ. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ መልስ ፈልጉ።

1. አለም አንድ መንደር እንድትሆን ያደረጋት ምንድን ነው?
2. አለም አንድ መንደር ሆናለች ሲባል ምን ማለት ነው?

3. ታሪካዊ ጉዳዮችን ቀርጸ ለትውልድ ለማቆየት የሚያገለግሉን መሳሪያዎች ምን ምን ናቸው?

**ለ. ለሚከተሉት በግል መልስ ፈልጉ። የግል መልሳችሁን በጥንድ ተወያዩበት።**

1. ዘመን ያፈራቸው ድጅታል መሳሪያዎች ጥቅም እንጂ ጉዳት የላቸውም
2. ድጅታል መሳሪያ የመልዕክት ልውውጥን ፈጣን አድርጎታል።
3. ከሜራ ታሪካዊና አይረሴ መረጃ መያዝ ያስችላል።
4. ዘመን ያፈራው መሳሪያ በጽሁፍና በድምጽ መልእክት መለዋወጥ ያስችላል።

## ክፍለጊዜ ሶስት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በቡድን ተነጋገሩ።

- በቤታችሁ ምን ምን የኤለክትሮኒክስ እቃዎች ይገኛሉ? ካሉት ውስጥ የግልና የጋራ የሆኑት የትኞቹ ናቸው።
- ለምን ለምን አገለግሎት ይውላሉ?

## ክፍለጊዜ አራት

### ተግባር ሁለት

ሀ. ታላላቆቻችሁ ስልካቸውን ለምን ለምን ይጠቀሙበታል? አጠቃቀማቸው ልክ ነው? ለምን? በቡድን ተወያዩበት።

ለ. የተነጋገራችሁበትን ልክ የሆነና ያልሆነ አጠቃቀም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር፡ ሦስት

ስራን በኮምፒዩተር የመስራት ጥቅም ምን እንደሆነ ከሚያውቅ ጠይቁ። ያገኛችሁትን ሀሳብ ለቡድናችሁ አቅርቡና ተወያዩበት። የተወያያችሁበትን ዋና ዋና ነጥብ በተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### መነጠል

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ከቃላቱ ላይ መነሻ ቅጥያዎችን ነጥሉ።

የሰራችሁትን ከሌላ ታማሪ ጋር አስተያዩ።

ምሳሌ ፡ትመጣለች ⟶ ት - መጣለች

1.ትሰፋለች 2. ይሄዳሉ 3.ተከመረ

4.ከታብሌት 5. ለሲም 6.ከድረገጽ

7.በኮምፒዩተር 8. የደወለ 9.በፌስቡክ

## ክፍለጊዜ ሰባት

ለ. የቃል መጨረሻ ቅጥያዎችን ነጥላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡ መጣች ⟶ መጣ-ች

1. መጣሽ
2. ሰራህ
3. ሄዳችሁ
4. በላን
5. ወሰደች
6. ኮምፒውተሮች
7. ታብሌትሽ
8. ስልክህ
9. ላፕቶፖች
10. ድረገጾች

## ክፍለጊዜ ስምንት

ሐ. መነሻ ቅጥያዎችንና መጨረሻ ቅጥያዎችን ነጥላችሁ ጻፉ።

| ቃል | መነሻ ቅጥያ | መጨረሻ ቅጥያ |
|---|---|---|
| ከስልካችን | ከ- | -ኣችን |
| በላፕቶፖች | በ- | -ኦች |
| የታብሌትሽ | | |
| በፌስቡካችሁ | | |
| በድረገጻቸው | | |
| ከቴሌቭዥኖችን | | |
| በድህረገጹ | | |

## ክፍለጊዜ ዘጠኝ

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ ሶስት

ሀ. በምሳሌው መሰረት ቃላትን ከተቃራኒያቸው ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. የግል | ሀ. በከባድ |
| 2. በአግባቡ | ለ. ለማዳከም |
| 3. በቀላል | ሐ. ያለአግባብ |
| 4. ለማጠናከር | መ. የቡድን |

**ለ. ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒያቸውን ስጡ።**

1. ጠቃሚ
2. ብርትታ
3. ለማጠናከር
4. ዘወትር
5. ጥንታዊ

## ክፍለጊዜ አስር

## መልመጃ አራት

**ለሚከተሉት ቃላት አገባባዊ ፍቺ ስጡ።**

1. በለጡ <u>ተንቀሳቃሽ</u> ስልኳን በአግባቡ ትጠቀማላች።

2. በስልካችን መረጃዎችን ከድረገፅ ማውረድ እንችላለን።
3. ለምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።
4. ስለታብሌት አጠቃቀም ትኩረት በመስጠት ግንዘቤ ማግኘት ይገባል።
5. ያወቁትን ለሌሎች ማካፈል ጥሩ ነው።
6. መረጃዎችን ከድረገጽ ማውረድ ይቻላል።

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

### ኮምፒውተር



## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. ከላይ ያለው ምስል የምንድን ነው?

2. በምስል የቀረበው መሳሪያ ለምን
   አገልግሎት ሊውል ይችላል?

## የማንበብጊዜ ጥያቄዎች

1. የዘመኑ______ከፈጠራቸው ነገሮች ውስጥ
   አንዱ ኮምፒውተር ነው።

2. ኮምፒውተር በ ____ እና በአገልግሎት
   እየተሻሻለ የመጣ መሳሪያ ነው።

3. ኮምፒውተርን እንደ _____ እቃ ማየት
   ቀርቷል።

ኮምፒውተር የዘመኑ ቴክኖሎጂ የፈጠረው የተለያየ አገልግሎት ያለው መሳሪያ ነው። ይህ መሳሪያ በመጠንም ሆነ በአገልግሎት እየተሸሻለ የመጣ ነው። በዚህ ዘመን

የኮምፒውተር ሳይንስ አድጓል። ኮምፒውተርን እንደ ቅንጦት እቃ ማየት ቀርቷል። እንዲያውም በየእለት የህይወት እንቅስቃሴ ውስጥ በጣም አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል። ለልጆችም፣ ለህጻናትም የሚመጥኑ የኮምፒውተር አይነቶች አሉ። ለሁሉም እንደ ደረጃቸውና እንደመጠቀም ብቃታቸው ተመጥኖ የተዘጋጀ መሳሪያ ነው። በመሆኑም የሰውን ልጅ የስራ ጫና በመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ያለ መሳሪያ ነው። መሳሪያው ለአጠቃቀም እንዲያመች ሆኖ የተዘጋጀ ነው። ኮምፒውተር ብዙ ስራ ይሰራበታል። ስራንም ፈጣንና ጥራት ያለው ያደርጋል።

# ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## መልመጃ፡ አምስት

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

**ትክክል የሆነውን ሀሳብ "እውነት" ያልሆነው "ሀሰት" በማለት መልሱ።**

1. ኮምፒውተር ስራን ያቀላል።
2. ኮምፒውተር ለዕለት ተዕለት አገልግሎት አይውልም።
3. ኮምፒውተር የሰውን ልጅ የስራ ጫና ይቀንሳል።
4. ኮምፒውተር ለህጻናት የሚሰጠው ጥቅም የለም።
5. ኮምፒውተር ስራን ያጓትታል።
6. ኮምፒውተር የስራን ጥራት ይጨምራል።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

### መልመጃ ስድስት

ከምንባቡ ውስጥ የተደጋገሙ ቃላትን ለዩ።

| የተደገመ ቃል | የድግግሞሽ ብዛት |
|---|---|
| መሳሪያ | 5 |
| | |

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

### ተግባር አራት

የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች በትክክል አንብቡ።

1. አሚና ዲጂታል መሳሪያዎችን ለይታ ታውቃለች?
2. እዝራ ሞባይሉን ለቁም ነገር ይጠቀምበታል።
3. ገመዳ ለትምህርቱ አጋዥ መጽሀፎችን ከድረገጽ አውርዶ ይጠቀማል?

4. ገነሜ ተንቀሳቃሽ ስልኳን በመጠቀም ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ታገኛለች?
5. ቴሌቭዥን ስልኮቻችን ላይ ያሉ መረጃዎች አተልቆ ለማየት ያስችላል።
6. ላፕቶፕሽን ለማን ሰጠሽ?
7. ስልክህ እንዳይጠፋ በጥንቃቄ ያዝ!
8. ወይ ጉድ! የይለፍ ቃሌን ማንነው የሰበረው?
9. የኮምፒውተሩን ቤት ቆልፈሃል?
10. ልብ አድርግ! ትላንት ያደረካትን እንዳትረሳ!

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## በጊዜ የተገደበ ንባብ

### ተግባር አምስት

### የአያንቱ ሞባይል

የአያንቱ ሞባይል ዘመናዊ ነው። በጣቶቿ መስታወቱን በመንካት ብቻ ትከፍተዋለች። ያለእሷ ፈቃድ ሌላ ሰው እንዳይከፍተው በይለፍ ቃል ትቆልፈዋለች። ስትፈልግ ምስጢራዊውን የስልኩን የይለፍ ቃል ተጠቅማ ትከፍተዋለች። ተንቀሳቃሽ ስልክ የግል መጠቀሚያ በመሆኑ ለሌሎች እንዲጠቀሙበት አትሰጥም። ክፍል ውስጥ ሞባይል ይዛም አትገባም። በአጋጣሚ እንኳ ይዛ ከገባች ድምጽ እንዳይኖረው ታደርጋለች።

# ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

## ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ

### መልመጃ ሰባት

ሀ. የተሰጡትን ስሥሎች በማየት

ምንነታቸውን ጻፉ።

| ስዕሎች | ስማቸው |
|---|---|
|  | |
|  | |
|  | |
|  | |
|  | |
|  | |

ለ. መምህራችሁ የሚነግሯችሁን ዐ. ነገሮች ጻፉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ ስምንት

ሀ. ግርግዳ ላይ ለተለጠፉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ጻፉ።

ለ. በአረፍተነገር ውስጥ ተዘበራርቀው የገቡትን ቃላት አስተካክላችሁ ደግማችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡ ጠዋት መጣ ትላንት ገመቹ ቤታችን

- ገመቹ ትላንት ጠዋት ቤታችን መጣ።

1. ደወለ በስልኩ ጫላ
2. በጥንቃቄ ጫልቱ ያዘች ስልኳን
3. መጠቀም ሱፋ አይችልም ኮምፒውተር
4. አልሰራም የቤት ትላንት ስራውን ከበደ

# ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ ዘጠኝ

በተሰጡት ቃላት አረፍተነገር ጻፉ።

1. ላፕቶፕ
2. ኮምፒውተር
3. ስልክ
4. ማውረድ
5. ድረገጽ

# ምዕራፍ አስር፡ የዱር እንሰሳት

## ክፍለጊዜ አንድ

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

### የአይጥ ንጉስ ልጅ



### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. ከምስሉ ምን ተረዳችሁ?
2. የአይጦች መኖሪያ የት ነው?
3. አይጥ ምን በማድረግ ትታወቃለች?

# የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

ሀ. በአዳመጣችሁት መሰረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. የአይጦች ንጉስ ለልጁ ሚስት እንድትሆን መጀመሪያ የጠየቀው የማንን ልጅ ነው?
2. ሽምግልናው እንዴት ሳይሳካ ቀረ?
3. የአይጥ ንጉስ ልጅ ምን ይመስላል?

## ክፍለጊዜ ሁለት

ለ. በአዳመጣችሁት መሰረት ለሶስት ተወያይታችሁ መልስ ስጡ።

1. ከሁሉም አይጦች መጥፎና ራሱንም ከሁሉም በላይ አድርጎ የሚያየው ማን ነው?

2.የአይጦቹ ንጉስ ልጁ የጭጋግን ልጅ
   እንዲያገባ የወሰነው ለምንድን ነው?
3.የአይጦቹ ንጉስ ለልጁ ለምን ከአይጦች
   ማጨት አልፈለገም?
4.ሽማግሌዎቹ ወደ ጭጋግ ቤት ለምን
   ሄዱ?
5.የአይጥ መንጋዎቹ እራሳቸውን እንዴት
   ይመለከታሉ?

ክፍለጊዜ ሶስት

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

### ተግባር አንድ

1. ስለምታውቁት የዱር አውሬ ለክፍል
   ጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉ።
2. የምታደንቁትን የዱር እንስሳ ለምን
   እንደምታደንቁ ግለጹ።

## ክፍለጊዜ አራት

### ተግባር ሁለት

ስለኒያላ ወይም አንበሳ ወይም ነብር ታሪክ ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ገለጻ አድርጉ።

## ክፍለጊዜ አምስት

### ተግባር ሶስት

አይጥ በሰው ላይ ስለምታደርሳቸው ጉዳቶች ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ንግግር አቅርቡ።

## ክፍለጊዜ ስድስት

## ትምህርት ሶስት፡ መነጠልና ማጣመር

### መልመጃ ሁለት

ሀ. በምሳሌው መሰረት ቃላት በሆሄያት

ነጣጥሉ።

ምሳሌ፡ ከረመ ⟶ ከ-ረ-መ

1. ዝሆን
2. ቀጭኔ
3. ነብር
4. አሳማ
5. ኒያላ
6. ድኩላ
7. ተኩላ
8. አነር
9. ሰጎን
10. ጥንቸል

## ክፍለጊዜ ሰባት

ለ. በምሳሌው መሰረት አጣምሩ።

ምሳሌ፡- በ-ከ-ተ ⟶ በከተ

1. ጅ-ብ
2. ጎ-ሽ
3. ሳ-ላ
4. ተ-ኩ-ላ
6. ከ-ር-ከ-ሮ
7. ዝ-ን-ጀ-ሮ
8. አ-ቦ-ሸ-ማ-ኔ
9. አ-ን-በ-ሳ

5. ቀ-በ-ሮ

10. አ-ው-ራ-ሪ-ስ

ክፍለጊዜ ስምንት

## ትምህርት አራት፡ የቃላት ጥናት

### መልመጃ ሶስት

ፊደላትን ባዶ ቦታ ላይ አስገቡና ቃላት መስርቱ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ነ | በ | ባ | ረ | ሻ | ወ | ቀ |

ምሳሌ፡-መ_ጠረ ⟶ መነጠረ

1. አ_ጠረ
2. ቀ_ጠረ
3. ጠ_ጠረ
4. አ_ጠረ
5. _ጠረ
6. _ጠረ

ክፍለጊዜ ዘጠኝ

### መልመጃ አራት

ሀ. የመጀመሪያ ፊደላቸውን በመተው አዲስ

ቃል መስርቱ።

ምሳሌ፡ መቁረጥ------ ቁረጥ

1. መምረጥ
2. መግደፍ
3. መሄድ
4. መንገር
5. መሳል
6. መንቀስ
7. መጻፍ
8. መውሰድ
9. መሳቅ
10. መውረድ

ለ. የመጨረሻ ፊደላቸውን በመተው አዲስ ቃል መስርቱ።

ምሳሌ፡ የሚያነበውን----- የሚያነበው

1. ግብር
2. አረባች
3. ሮጠች
4. መጣን
5. አገኘሁ
6. ጨሉሌዋ

ክፍለጊዜ አስር

## መልመጃ አምስት

በምሳሌው መሰረት የመነሻ ፊደል መተካት ቃል መስርቱ።

ምሳሌ፡ አገባ---ገነባ

1. ውዳሴ
2. ጸጥታ
3. ሰከነ
4. ብርድ
5. ጎርፍ

## ክፍለጊዜ አስራ አንድ

### መልመጃ ስድስት

በምሳሌው መሰረት የመጨረሻ ፊደል በመተካት ቃል መስርቱ።


ምሳሌ፡ ሰበረ-ሰበከ

1. ወቀጠ
2. ከመረ
3. ሰከነ
4. መረጠ
5. ቀጠፈ

# ክፍለጊዜ አስራ ሁለት

## ትምህርት አምስት፡ ማንበብ

### ዝሆንና ሌሎች እንሰሳት



## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

1. ዝሆን ከሌሎች የዱር እንሰሳት በምን የሚለይ ይመስላችኋል?
2. ዝሆን ምን የሚመገብ ይመስላችኋል?

## የማበብጊዜ ጥያቄዎች

1. የለሊት ወፍ ለምን አትራመድም?
2. የዝሆን የእርግዝና ጊዜ ምን ያህል ነው?
3. ቀጭኔ የራሱን ጆሮ የሚያጸዳው በምንድን ነው?

## ምንባብ፡ የዝሆንና የሌሎች እንሰሳት አስደናቂ ነገሮች

የዝሆን የእርግዝና ጊዜ ሁለት አመት ነው። ቀጭኔ የራሱን ጆሮዎች የሚያጸዳው 21 ኢንች በሚረዝመው ምላሱ ነው። የሰጎን አይን ትልቅነት ከአንጎሏ ይበልጣል። በተለምዶ ጎሬላ የሚባሉት ግዙፍ የጦጣ ዝርያዎች ሰዎችን የሚይዛቸው ጉንፋን እንዲሁም ተመሳሳይ በሽታ ይይዛቸዋል።

የለሊት ወፍ እግር እጅግ በጣም ቀጭን ከመሆኑ የተነሳ የትኛውም የሌሊት ወፍ መራመድ አይችልም።

## መልመጃ ሰባት

1. የምንባቡን ዋና ዋና ነጥቦች ዘርዝሩ።
2. "ዝሆንና ሌሎች እንሰሳት" ከሚለው ምንባብ መረጃዎችን በጽሁፍ አቅርቡ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሶስት

## ተግባር አራት

**በትክክለኛ ቅላጼና ፍጥነት አንብቡ።**

ካንጋሮ ጭራዎቹ መሬት ሳይረግጡ መዝለል አይችልም። ፒንጉይኖች ባይበሩም እስከ 2 ሜትር ከፍታ መዝለል ይችላሉ። የሜዳ

አህዮች ልክ እንደ ጣት አሻራ ያላቸው የጥቁርና ነጭ መስመር የተለያየ ነው። ከአጥቢ እንስሳት መዝለል የማይችለው ዝሆን ብቻ ነው። ሰጎኖች 42 "ኪ.ሜ በሰዓት ይሮጣሉ። ወንድ ሰጎን ደግሞ እንደ አንበሳ ያገሳል።

## ክፍለጊዜ አስራ አራት

## ተግባር አምስት

**በደቂቃ ምን ያህል ቃላትን በትክክል ማንበብ እንደምትችሉ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተገማገሙ።**

በድሮ ጊዜ አንድ ወንዝ አጠገብ ካለ ዛፍ ላይ የምትኖር ጦጣ ነበረች። ጦጣዋም ከዛፉ ላይ የምታገኘውን ጣፋጭ ፍሬ እየበላች ትኖር

ነበር። ከእለታት አንድ ቀን በወንዙ ውስጥ ይኖር የነበረ አንድ አዞ ጦጣዋ አንዷት ፍሬ እንድትወረውርለት ጠየቃት። ጦጣዋም አንድ ፍሬ ወረወረችለትና አዞውም ፍሬውን ሲበላ በጣም ስለጣፈጠው "እባክሽ አንድ ጨምሪልኝ" ሲላት ጦጢትም በድጋሚ አንድ ወረወረችለት።

## ክፍለጊዜ አስራ አምስት

## ትምህርት ስድስት፡ መጻፍ

## መልመጃ ስምንት

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አንብቡና ተገቢውን ቃለአጋኖ ወይም የጥያቄ ምልክት አስገቡ።

ምሳሌ፡- እሰይ___ ከቤ መጣ።

እሰይ! ከቤ መጣ።

1. ዋ __
2. መቼ መጣህ__
3. አቤት __
4. በምን መጣህ__
5. ወይጉድ__ እንዴት ጎበዝናት__

## ክፍለጊዜ አስራ ስድስት

### መልመጃ ዘጠኝ

1. እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ያሉትን የዱር እንሰሳት በዝርዝር ጻፉ።
2. ሰለ ዱር እንሳሳት አረፍተነገሮች ጻፉ።

## ክፍለጊዜ አስራ ሰባት

### መልመጃ አስር

**የቃላቱን ቅድም ተከተል በማስተካክል አረፍተነገር ጻፉ።**

ምሳሌ፡ዝጋው ፊይሳ በሩን ---

ሲስተካከል፣ *"ፈይሳ በሩን ዝጋው!"*

ይሆናል

1. አለሚቱ ስንተኛ ወጣች
2. ከማል ሄደ ወዴት
3. እባክህ አትጨህብኝ
4. ተቀመጥ አርፈህ
5. ቤት መጣች ጫልቱ ጠዋት ከትምህርት
6. በልቶ ቁርስ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ

## ክፍለጊዜ አስራ ስምንት

## መልመጃ አስራ አንድ

**በሚከተሉት ቃላት አረፍተነገር ጻፉ።**

| | | |
|---|---|---|
| 1. ዱር | 2.አውሬ | 3.ዳዋ |
| 4. ኩምቢ | 5. ፈጣን | 6.ቅጠላቅጠል |